የአማራ ኅብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ | Amhara Heritage Society of Minnesota
1861 University Ave W, St. Paul, MN 55104 Suit S-340
Ph: 763-291-2501 email: amharaMN@gmail.com www.amharaMN.org

October 27, 2019 Ref. # PR0001

# የአቋም መግለጫ

ባለፉት ጥቂት ቀናት በኢትዮጵያ የኦሮሞ ክልላዊ መስተዳደር ውስጥ የተደረገውን ጭካኔ የተሞላበት እና ሰብዓዊነት የጎደለው የጅምላ ጥቃት እና የሰዎች ነፍስ ማጥፋት በሚያሳዝን ሁኔታ ታዝበናል።

በስልጣን ናፋቂው እና “የመብት ተሟጋች” ተብዬው ጀዋር መሐመድ እና በሱ በታወሩት ተከታዮቹ አማካኝነት እ.አ.አ ጥቅምት 23, 2019 ዓ.ም. የተፈጸመውን የህይወት መጥፋት፣ የንብረት መውደም እና በህብረተሰቡ ላይ የተፈጠረውን ጭንቀት እና ሽብር አጥብቀን እንቃወማለን። የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት ከላይ ለተጠቀሱት ጥፋቶች ሁሉ ጃዋር መሐመድን፣ የኦሮሞ ሚድያ ኔትወርክን(OMN) እንዲሁም ኃላፊነት የጎደላቸውን የመንግሥት ባለሥልጣናትን ተጠያቂ እንዲያደርግ አጥብቀን እንጠይቃለን።

በበለጠ የሚያሳዝነው የኦሮሞ ማኅበረሰብ በሚኒሶታ አመራሮች ለጀዋር መሐመድ ያላቸውን አጋርነት በመግለጽ ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት ጀዋርን እና ብሔረሰባቸውን በተለየ ሁኔታ የሚጠብቁ እርምጃዎችን እንዲወስድ ጠይቀዋል።

“እሳት ቢያንቀላፋ ገለባ ጎበኘው” እንዲሉ በሚኔሶታ ያሉ የኦሮሞ ማኅበረሰብ አመራሮች የአማራው ኅብረተሰብ እና ባጠቃላይ ኢትዮጵያውያን የመጣውን ለውጥ ለማገዝ በማለት ያሳዩትን ከፍተኛ ጥረት እና ትዕግስት ለመገምገም እና ለመረዳት ጥበቡ እና ችሎታው እንደሌላቸው ያሳያል።

የአማራ ሕዝብ ላለፉት 50 ዓመታት እና ከዛም በላይ በአክራሪ ብሄረተኞች እና አክራሪ የእምነት ቡድኖች ሲገፋ ኖሯል። ምንም እንኳን በአማራ ላይ ጭካኔ የተሞላበት ግፍ ቢፈጸም እና መከራ እና ስቃዩ  ቢበዛም ማንነቱን ጠብቆ እንደማይታይ ሙጫ እራሱን እና በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያንን በአንድነት ይዞ ቆይቷል። አማራዎች ኢትዮጵጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን በመገንባት ላይ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። እራሳቸውን ከማንም በላይ ከፍ ሳያደርጉ ግብረገብ እና ስነምግባር በሞላው መንፈስ ከሌሎች ውንድሞቻቸው ጋር በመሆን የአገራቸው ጠባቂ እና ባለድርሻ ሆነው ቆይተዋል። ባሁኑ ወቅት በሌሎች እንደሚታየው “ሁሉ እኛ ነን እኛ፣ ሁሉም የኛ ነው” የሚለው አሳፋሪ ግብዝነት አማራው የሚጸየፈው ተግባር ነው።

## አሁን ግን በቃ ሲል በቃ  ነው!!!

ስለዚህ እኛ የአማራ ማኅበረሰብ ቅርስ በሚኒሶታ የሚከተሉት ነጥቦች በአስቸኳይ እንዲሟሉ በአጽንዖ እንጠይቃለን፡-

**፩.** በኦሮሞ ክልላዊ መስተዳደር ውስጥ በአማራዎች እና በሌሎች አማርኛ በሚናገሩ ኢትዮጵያዊያን ላይ የሚደርሰው ጥቃት፣ ግድያ እና ሽብር በአስቸኳይ እንዲቆም።

**፪.** “የመብት ተሟጋች” ነኝ ባዩ ጃዋር መሐመድ እና ሌሎች በኢትዮጵያም ሆነ በውጪ አገር የሚኖሩ ለኦሮሞ መብት ቆመናል የሚሉ ግለሰቦች እና የኦሮሞ ኮሚዩኒቲ አመራሮች እንዲሁም ገንጣይ እና ጽንፈኛ የኦሮሞ ፖለቲከኞች በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳደር ውስጥ የሚኖሩ አማራዎችን እና አማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያዊያንን በማግለል፣በመግደል እና ሽብር በመፍጠር እየፈጠሩ ካሉት እኩይ ተግባር እንዲታቀቡ።

**፫.** ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ(አብን) የፖለቲካ መሪዎች፣ ደጋፊዎች፣ ጋዜጠኞች እንዲሁም የአዲስ አበባ ባለ አደራ ምክር ቤት(ባልደራስ) አመራር አባላት እና ደጋፊዎች ከእስር እንዲፈቱ።

**፬.** የሀሰት ትርክቶችን እና እውነትነት የጎደለውን ታሪክ በማናፈስ ዓለም አቀፋዊ የሆነችውን የአገራችንን  ዋና ከተማ አዲስ አበባን እንዲሁም የተወሰኑ በአማራ ክልል የሚገኙ የአማራን ግዛቶች የኦሮሞ ናቸው የሚል ግብዝ የይገባኛል እና ጸብ-አጫሪ ጥያቄ በማንሳት፣ ገናና ታሪክ ያላትን

ባለ ብዙ ታሪክ ባለቤት የሆነችውንና በብዙ አገሮች ዘንድ የነጻነት መብራት በመባል የምትታወቀዋን አገራችን ኢትይዮጵያን ከውጭ ወራሪ በመከላከልና በመንከባከብ ያቆዩንን ጀግኖቻችንን በማጥላላትና ስማችውን በማጉደፍ እና የጥላቻ ንግግሮች በማሰራጨት የሚደረገው ጸብ ቀስቃሽ ተግባር ባስቸኳይ እንዲቆም።

፳. የሀይማኖት ግጭቶን የሚፈጥሩ ትንኮሳዎች እንዲቆሙ፤ በተለይ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን እምነት ተከታዮችን ዒላማ በማድረግ የሚካሄደው ነፍስ በማጥፋት ባስቸኳይ እንዲቆም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያንን እና የእምኑቱ ተከታዮች በታሪክ የከፈሉትን መስዋትነት ሳይጠቅሱ ስለ ኢትዮጵያ ማውራት አይቻልም።

፳፩. በመጨረሻ ነገር ግን በዋናነት በጠቅላይ ምኒስትር ዶ/ር አብይ አሕመድ የሚመራው የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት በእኩልነት የተመሰረተ አስተዳደር እና የህግ የበላይነትን በአስቸኳይ በመላ ኢትዮጵያ እንዲያሰፍን!!!

## አንድ አማራ ለሁሉ አማራ - ሁሉ አማራ ለአንድ አማራ!!!

## ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## ከአማራ ቅርስ ማኅበረሰብ የህዝብ ግንኙነት ክፍል።